# ጨልሞ፣ ጨልሞ፣ አይነጋም መስሏችሁ!

ከመብረቁ ዘቋራ

ያለቅጥ ከረፋ፣ ታሪክ በጣም ገማ!
ልብ ያለህ አስተውል፣ ጆሮ ያለህ ስማ!

በወያኔ ዘመን፣ አይሰማ የለ፣
“ዋልድባ ለአማራው፣ ምኑ ነው?” ተባለ?!
እረ እነ አቶ መለስ፣ እየተስተዋለ!
ተከዜን ተሻግሮ፣ የትግሬ ቀዬ አለ?!
“ጊዜ የሰጠው ቅል፣ ድንጋይ ይሰብር" የለ?
ይኸ ጭፍን መስካ፣ ቢበቃ ምን አለ?!

ከተከዜ ግድብ፣ በመነጨው መብራት፣
እረ ለመሆኑ፣ ማነው የሚያዝበት?

የኢትዮጵያ ሕዝብ፣ በከፈለው ዋጋ፣
ትግራይን ለማልማት፣ መረብ ተዘረጋ?!
ይህንን አያውቅም፣ ኢትዮጵያዊ ዜጋ?!
ሁሉንም ለትግራይ፣ ወይነገር ፍለጋ!
አያሳስብም ወይ፣ የነገው አደጋ?

መብራቱም ለትግራይ፣ ባቡሩም ለትግራይ፣
ሌላው የኢትዮጵያ፣ ሀገር አይደለም ወይ?!

ፀለምት፣ ወልቃይትን፣ ጠገዴን ወራችሁ!
የወገራን አካል፣ ሁመራን ቆርጣችሁ!
ለትግራይ በሱዳን፣ ወሰን ከልላችሁ፣
'ሁመራ ለጎንደር፣ ምኑ ነው?” አላችሁ?!
ጨልሞ፣ ጨልሞ፣ አይነጋ መስሏችሁ?!

ያንዬ በእንግድነት፣ ችግር ጠንቶባችሁ፣
የወልቃይትን ማር፣ የጠገዴን ቅቤ፣ ስለለመዳችሁ፣
ወራሪ ነፍጠኛ፣ ተምች አሰፈራችሁ!
ያባወራውን ቤት፣ እየደፈራችሁ!
አገሩን በሙሉ፣ የእኛ ነው አላችሁ?!
መች እንዲህ ነበረ፣ የአባት አደራችሁ!

ጨልሞ፣ ጨልሞ፣ አይነጋ መስሏችሁ!
ዘርን የሚያጠፋ፣ ዘር ትዘራላችሁ?!
የምትሰሩትን ግፍ፣ ጊዜ ይፍረዳችሁ!
ከቶ ከየትኛው፣ ዘር ተፈጠራችሁ?!
እውን ወያኔዎች! የትግራይ ዘር ናችሁ?!

ከሁመራ ወዲያ፣ እስከ ኢሉባቦር፣
ሸርፋችሁ፣ ሸርፋችሁ፣ ያገሪቱን ድንበር፣
አንድ ጥይት ሳይጮህ፣ ለሱዳን መገበር፣

ይህ ዓይነት ማፈግፈግ፣ ይገባችሁ ነበር?!
በኢትዮጵያ፣ ባለፉት መንግሥታት፣
ታይቶ አይታወቅም፣ እንዲህ ያለ ፍርሃት።
ቴዎድሮስ፣ ምኒልክ፣ ዮሐንስ ሰማዕቱ፣
ይህን ሳይሰሙ፣ እንኳን ቀድመው ሞቱ!

ወያኔ፣ ኢሕአዴግ፣ ኢትዮጵያዊነቱ፣
አልታየኝ አለ፣ የት ነው ምልክቱ?
በሰሜን፣ በደቡብ፣ በምዕራብ፣ በምሥራቅ፣
አገሩን የሚሸጥ፣ አገሩን የሚሰርቅ!
ኢትዮጵያዊ አይደለም፣ ይህ ዓይነቱ ጭራቅ!
መወገድ አለበት፣ ገና ጀምበር ሳትጠልቅ!
ሕዝብ ኀብረትህን አጥና፣ አትሰነጣጠቅ!

የጊዜ ጉዳይ ነው፣ ቃሉ አይታበልም፣
"በሠራዊት ብዛት፣ ንጉሥ ድኖ አያውቅም፣"
(መዝሙረ ዳዊት፣ 32፥ 16-17 ያንብቡት)
"ብዙ ሰው እግዜር ነው፣ የሚሳነው የለም።"

ግንቦት 2004 ዓ. ም.